## ሙርናሉንግ ፓርክ (Murnalung Park) የእንቅስቃሴ ማእከል ይሆናል



**'ሙርናሉንግ' ወደ ፍሌሚንግተን የሚመጣው የአዲሱ ማዕከላዊ ፓርክ ስም ነው።**

በዓመቱ አጋማሽ ላይ ይከፈታል ተብሎ የሚጠበቀው ይህ ፓርክ ከ5,000 ካሬ ሜትር በላይ አረንጓዴ ክፍት ቦታ ለህዝብ ጥቅም ያውላል።

የሙርናሉንግ ፓርክ የተሰየመው ከዉሩንጄሪ ዎይ-ዉሩንግ ሽማግሌዎች ጋር በመተባበር ሲሆን ትርጉሙም 'ንብ' ማለት ነው፣ ምክንያቱም ፓርኩ የእንቅስቃሴ ቀፎ ወይም ማእከል እና ለነዋሪዎች እና ለማህበረሰቡ ማዕከላዊ የመሰብሰቢያ ቦታ ይሆናል።

ሙርናሉንግ ፓርክ በተቋቋሙ ወይም በቆዩ ዛፎች፣ የአትክልት ስፍራዎች፣ ትልቅ የልጆች መጫወቻ ቦታ፣ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ጣቢያ እና መቀመጫ እና መላው ማህበረሰብ የሚዝናናባቸው የሽርሽር ጠረጴዛዎች መካከል በሳር የተሸፈኑ ቦታዎችን ያቀርባል።

### እንደተገናኙ መቆየት

የመረጃ ክፍለ ጊዜያት

የምክክር አስተያየት

ወቅታዊ መረጃዎችን ለማግኘት ይመዝገቡ

ተሳታፊ ሆኖ ለመቆየት ከታች ያለውን ይጎብኙ፦

homes.vic.gov.au/flemington-precinct



በማህበራዊ ሚዲያዎች ላይ **Homes Victoria** ብለው በመፈለግ ይከተሉን

## በፍሌምንግተን ውስጥ ምን እየሆነ ነው

### 126 ሬስኮርስ ሮድ (Racecourse Road)

- የአየር ኮንዲሽነር መገጠሙን ቀጥሏል
- ደህንነቱ የተጠበቀ የማይንሸራተት ወለል ለመፍጠር (እንዲሁም በ130 ሬስኮርስ ሮድ/Racecourse Road ላይ በመካሄድ ላይ ነው) ደረጃዎች እና ማረፊያዎች በመቀባት ላይ ናቸው

### የኒው ሆላንድ ኮርት (New Holland Court) ልማት

- የቅዳሜና የእሁድ ሥራ ከጠዋቱ 7 ሰአት እስከ ምሽቱ 5 ሰአት ድረስ ይቀጥላል

### የኤሌክትሪክ እና የውሃ ግንኙነቶች ለወደፊቱ አስተማማኝ ለማድረግ

- ነባር አገልግሎቶችን ማግኘት እና አዲስ ከወለል በታች ያሉ አገልግሎቶችን መትከል
- የላይኛው መብራት ማስወገድ እና ማዛወር
- የቁፋሮ እና የመጋዝ መሳሪያዎችን እና ከባድ ተሽከርካሪዎችን በቦታው ትመለከቱ ይሆናል
- በመንገዶች፣ በመኪና ማቆሚያ መዳረሻ እና በእግረኛ መንገዶች ላይ አንዳንድ ለውጦች ይኖራሉ
- በ130 ሬስኮርስ ሮድ ላይ ተደራሽ የመኪና ፓርኮች ወደ ምስራቃዊ የመኪና ማቆሚያ ይተላለፋሉ
- እንቅፋቶች ይኖራሉ ስለሆነም  ደህንነትዎን ለመጠበቅ በአካባቢው መብራት በደንብ ይበራል
- ወደሚፈልጉበት ቦታ ለመድረስ እንዲችሉ ምልክት ይደረጋል
- በ130 ረኢስኮርስ ሮድ እና በሬስኮርስ ሮድ መግቢያ መካከል ያለውን ተደራሽነት ለመጠበቅ ስራዎች በየደረጃው ይከናወናሉ

በቋንቋዎ የተጻፈ መረጃን ጨምሮ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የሚከተሉትን ይጎብኙ - **homes.vic.gov.au/information-in-your-language**

በቪክቶሪያ መንግስት የተፈቀደ እና የታተመ ፣ 1 Treasury Place, Melbourne.
© State of Victoria, Homes Victoria፣ ሜይ 2026። (HV013126)።
በFinsbury Green, Melbourne Victoria, 3000 የታተመ።

## በ12 የሆላንድ ኮርት እና በ120 ሬስኮርስ ሮድ ምን እየሆነ ነው

- ለደህንነት የስራ ቦታውን ማስተካከል እና ምልክቶችን ማስቀመጥ
- የአገልግሎት ግንኙነቶችን መፈተሽ
- ለእግረኞች፣ ለመኪናዎች እና ለመኪና ማቆሚያዎች ደህንነቱ የተጠበቀ መዳረሻን ማመቻቸት
- ደህንነታቸውን ለመጠበቅ በህንፃዎች ውስጥ እየሰራን ነው
- ባዶ በሆኑ አፓርታማዎች እና በአንዳንድ ደረጃዎች የሚገኙ የኮንክሪት ቁሳቁሶችን ለመመርመር አንዳንድ ቁፋሮዎች ይካሄዳሉ
- ቁም ሣጥኖችን፣ የወለል ንጣፎችን እና ሌሎች ትናንሽ እቃዎችን ከባዶ አፓርታማዎች ማስወገድ
- ትርጉም በሚሰጥበት መልኩ የኤሌክትሪክ ዕቃዎችን እንደገና ጥቅም ላይ ማዋል

ስራችን የሚመራው በምክር ቤትዎ መደበኛ የስራ ሰዓታት ነው፦

| **ከሰኞ እስከ አርብ** | **ቅዳሜ** |
|---|---|
| ከጠዋቱ 7 ሰዓት እስከ ምሽቱ 6 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ | ከጠዋቱ 9 ሰዓት እስከ ምሽቱ 3 ሰዓት |

አንዳንድ ጊዜ ከእነዚህ ሰዓታት ውጭ ለመስራት የምክር ቤት ፈቃድ ያስፈልጋል፤ ነገር ግን ይህ ከተከሰተ ለነዋሪዎች እናሳውቃለን።

ሁሉም ስራዎች በከፍተኛ የደህንነት ደረጃዎች እና ህጋዊ መስፈርቶች ይከናወናሉ።

ተጨማሪ መረጃ ለሚፈልጉ ነዋሪዎች የአካባቢዎን የመኖሪያ ቤቶች ቢሮን ያነጋግሩ፦

**1300 360 462**

**ascotvale.housing@dffh.vic.gov.au**

ለአጠቃላይ ጥያቄዎች የኢሜይል ኣድራሻ:

**enquiries@homes.vic.gov.au**

More Homes For Victorians | VICTORIA State Government

Amharic | አማርኛ

ሜይ 2026

homes victoria

**ታላቁ የመኖሪያ ቤት ግንባታ**

# ፍሌሚንግተን

## የማህበረሰብ ወቅታዊ መረጃ



### ፍሌሚንግተንን በበለጠ እና በተሻሉ ቤቶች መለወጥ

በፍሌሚንግተን ውስጥ ከ800 በላይ አዳዲስ ቤቶችን እና የተለያየ ጥቅም የሚሰጡ የማህበረሰብ ቦታዎችን ለማቅረብ በእቅድ ደረጃ ላይ ነን

### ምክክር አሁን ተከፍቷል

ረቂቅ እቅዶቹን ይመልከቱ እና እስከ እሁድ ሰኔ 7 ድረስ ግብረመልስ ይስጡ

### ሙርናሉንግ ፓርክን/Murnalung Park ማስተዋወቅ

5,000 ካሬ ሜትር ስፋት ያለው የህዝብ አረንጓዴ"ቦታ ለፍሌሚንግተን

ሆምስ ቪክቶሪያ/Homes Victoria የአቦርጂናል እና የቶረስ ስትሬት ደሴት ነዋሪዎችን የምድሪቱ ባህላዊ ጠባቂዎች አድርጎ ይቀበላል እና ያለፉትን እና የአሁኑን ሽማግሌዎቻቸውን እውቅና ይሰጣል ብሎም ያከብራል።

## የፍሌሚንግተን መኖሪያ ቤት ለውጥ ሽግግር ቀጥሏል

**በፍሌሚንግተን አከባቢ ለማህበረሰብ፣ ለችርቻሮ እና ለብዙ ቪክቶሪያውያን አገልግሎቶች የሚሆኑ ብዙ ቤቶችን እና ቦታዎችን ለመስራት ቀጣዩን ትልቅ እርምጃ ወስዷል እቅድ ማውጣትም ተጀምሯል።**

ትልቁ የቤቶች ግንባታ (The Big Housing Build) በፍሌሚንግተን በመቶዎች የሚቆጠሩ አዳዲስ ቤቶችን አቅርቧል፣ እና ለቀጣዩ ደረጃ ከ800 በላይ አዳዲስ ቤቶች ለማቅረብ ታቅዷል።

በረቂቅ ዲዛይኖቹ የተሰጠው አስተያየት በራዕይ ተሳትፎ ወቅት አድምጠናል ነዋሪ እና ማህበረሰብ በዚህ መልኩ ግብአት በቀጥታ ምላሽ ሰጥተዋል። ሁሉም መጠን ያላቸውን ቤተሰቦች ለመደገፍ እስከ አምስት መኝታ ቤቶች የሚደርሱ ጥራት ያላቸው ኃይል ቆጣቢ ቤቶችን ያካትታሉ። የቆዩ ሰማይ ጠቀስ ፎቆችን እንደገና በምንገነባበት ወቅት በአካባቢው ለመቆየት የሚፈልጉ ነዋሪዎችን ለመደገፍም ይገኛሉ።

በታቀዱት ዲዛይኖች ውስጥ እያንዳንዳቸው የተስተካከለ የአትክልት ገጽታ ያለው የጋራ ክፍት ቦታ እና ለነዋሪዎች ምርታማ የአትክልት ቦታዎች ያሉት የፎቅ መድረክ ወይም ቦታ አላቸው።

ሁለገብ የማህበረሰብ ቦታዎች፣ እንዲሁም ለካፌዎች፣ ለሱቆች ወይም ለጤና አገልግሎቶች የሚሆኑ ቦታዎች ሁሉም የረቂቅ ዲዛይን አካል ናቸው። በሬስኮርስ ሮድ/Racecourse Road ላይ ለአዲስ መገበያያ ሱፐርማርኬት የሚሆን ቦታም ይኖራል።

አዲስ፣ በደንብ ብርሃን ያላቸው ጎዳናዎች፣ የእግረኛ እና የብስክሌት መንገዶች ሰፈሩን በተሻለ ሁኔታ ያገናኛሉ።

**አሁን ህብረተሰቡ በረቂቅ እቅዶቹ ላይ አስተያየት እንዲሰጥ እንጋብዛለን።**

### ደረጃ 1 እድሳት



**ቪክቶሪያ ስትሪት (Victoria Street)**
359 አዳዲስ ቤቶች እና አዲስ የማህበረሰብ ቦታዎች
**በ2023 ተጠናቅቀዋል**

### ደረጃ 2 እድሳት



**ሆላንድ ኮርት (Holland Court)**
286 አዳዲስ ቤቶች እና አዲስ የማህበረሰብ ቦታዎች
**በ2026 መገባደጃ ላይ ይጠናቀቃሉ**

### ምክክር አሁን ተከፍቷል

ከ800 በላይ አዳዲስ ቤቶችን እና የተለያየ ጥቅም ላይ የሚውሉ የማህበረሰብ ቦታዎችን ረቂቅ እቅዶችን ይመልከቱ።

ስለ ፕሮጀክቱ የበለጠ ይወቁ፣ ለማህበረሰብ መረጃ ክፍለ ጊዜዎች ቀኖችን እና ሰዓቶችን ይመልከቱ ወይም አስተያየትዎን ድረገጽ መስመር ላይ በቀጥታ ያቅርቡ። **https://engage.vic.gov.au/racecourse-road-flemington-housing** ይጎብኙ ወይም የQR ኮድን ስካን ያድርጉ።

## የሚቀጥለው የእድሳት ደረጃ



**የሬስኮርስ ሮድ ግንባታ**

- የፎቅ/የጣሪያ መድረክ የነዋሪዎች ላውንጅ
- ለመሰብሰብ እና ለመዝናናት የተስተካከሉ የአትክልት ስፍራዎች
- በመጨመር ላይ ያሉ የጋራ ቦታዎች



**ሙርናሉንግ ፓርክ**

- አዲስ 5000 ካሬ ሜትር ማዕከላዊ ፓርክ በ2026 አጋማሽ ይከፈታል



**ዴብኒስ ፓርክ/Debneys Park ግንባታ**

- ከ400 በላይ አዳዲስ ማህበራዊ ቤቶች እስከ 5 መኝታ ክፍሎች ድረስ
- እስከ 100 ሰዎች መያዝ የሚችል ቦታን ጨምሮ ሶስት ሁለገብ የማህበረሰብ መገልገያ ክፍሎች
- በቦታው ላይ የተከራይ አስተዳደር
- የመኪና ማቆሚያ እና የብስክሌት መጋዝን
- የህክምና እና የጤና አገልግሎቶችን ጨምሮ ለሱቆች እና አገልግሎቶች ቦታዎች






**የሬስኮርስ ሮድ ግንባታ**

- የቪክቶሪያን የመኖሪያ ቤት ፍላጎቶች በቀጥታ የሚያሟሉ ከ400 በላይ ዘመናዊ እና ኃይል ቆጣቢ የኪራይ ቤቶች
- መጠናቸው የተለያየ እስከ 4 መኝታ ቤቶች
- የወደፊቱን ሱፐርማርኬት ለመደገፍ ለነዋሪዎች የመኪና ማቆሚያ እና የብስክሌት መጋዝን እና ተጨማሪ የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች ይሰራሉ
- በሬስኮርስ ሮድ ላይ ለሱፐርማርኬት የሚሆን ቦታን ጨምሮ ለሱቆች፣ ካፌዎች እና አገልግሎቶች ምድር ቤት ያሉ ቦታዎች



**ዴብኒስ ፓርክ/Debneys Park ግንባታ**

- ለመሰብሰብ እና ለመዝናናት የሚሆኑ የፎቅ/የጣሪያ መድረክ ቦታዎች
- በመጨመር ላይ ያሉ የተስተካከለ ገጽታ ያላቸው የአትክልት ስፍራዎች
- የነዋሪዎች መቀመጫ ላውንጅ